የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 19
ADDIS ABABA - 13th January, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፩/፲፱፻፺፪ ዓ·ም·
የኢትዮ – ሊቢያ የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስ ፡ የባሕልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፩ሺ፪፻፴፮

## CONTENTS

Proclamation No. 191/2000
Ethio-Libya Economic, Scientific, Cultural and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation ........................................ Page 1236

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፩/፲፱፻፺፪

### የኢትዮ – ሊቢያ የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስ ፡ የባሕልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በታላቋ የሊቢያ ሕዝባዊት ሶሻሊስት አረብ ጀማሂሪያ መንግሥታት መካከል የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስ ፡ ባሕልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት እ·ኤ·አ· ሜይ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፱ በታላቋ ጀማሂሪያ ሲርቴ ከተማ ላይ የተፈረመ ስለሆነ፡

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋዮቹ አገሮች ሕጐች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ልውውጥ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮ–ሊቢያ የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስ ፡ የባሕልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፩/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 191/2000

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO-LIBYA ECONOMIC, SCIENTIFIC, CULTURAL AND TECHNICAL COOPERATION AGREEMENT

WHEREAS, an Agreement, on Economic, Scientific, Cultural and Technical Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great Socialist People's Libya Arab Jamahirya, was signed at the City of Sirte of the Great Jamahirya, on the 17th day of May, 1999;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement is subject to ratification according to the legal procedures of each country, and enter into force upon the date of the exchange of instruments of ratification;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 13th day of January, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethio-Libya Economic, Scientific, Cultural and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 191/2000."

፪· <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በታላቋ የሊቢያ ሕዝባዊት ሶሻሊስት አረብ ጀማሂሪያ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ሚይ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ሲርቴ ከተማ ላይ የተፈረመው የኢኮኖሚ ፣ የሣይንስ ፣ የባሕልና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል ።

፫· <u>የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፬ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥር ፬ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on Economic, Scientific, Cultural and Technical Cooperation Signed in Sirte on the 17th day of May, 1999, between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great Socialist People's Libyan Arab Jamahirya, is ratified.

3. *Power of the Minister of Economic Development and Cooperation*

The Minister of Economic Development and Cooperation is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 13th day of January, 2000.

Done at addis Ababa, this 13th day of January, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE